ሰኔ 12/1999 ዓም/ጁን 18 2007

# <u>በቅሎ አባትሽ ማነው ቢሏት ፈረስ አጎቴ ነው አለች</u>

(3ኛና የመጨረሻ ክፍል)

ከአያልነሽ

ሰሞኑን በስብሃት ነጋ የአብሪት አዋጅ ላይ በተከታታይ ሳቀርበው የነበረውን "የእንደምስሳችኋለን" ዛቻ፣ 3ኛና የመጨረሻውን ክፍል አቅርቤ ልሰናበታችሁ። ምናልባት በዚህ ተከታታይ ጽሁፌ አንባቢዎቼን አድክሜ/ግዜአችሁንም ተሻምቼ ከሆነ ታላቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ። በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል፣ ተብሎ የለ! ያጋጠመኝ ችግር ያ ሆኖብኝ ነው። የወያኔ ባለስልጣኖች "<u>ልንገነባት</u> <u>የምናስበው አዲሲቱ ኢትዮጵያ</u> " በሚለው ቋንቋቸው እስከዛሬም ሊነግሩን የደከሙት "የድሮው ኢትዮጵያዊነት አባዜን አስትተን/አጥፍተን" ለአዲሱ ትውልድ ልናስተላልፈው የምንሻው "የደቀቀች አገር የሚመኙ፣ ያልነበረች አገር የሚያቀነቅኑ በጣም ጥቂት" የሆኑ ሰዎችን ጨፍልቀን "አዲሱን የኢትዮጵያዊነት በረከት" ለአብዛኛውና ለአዲሱ ትውልድ ለማላበስ ነው ይላሉ።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ሆይ!

የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት) መስራቾችና የድርጅቱን አለቆች ከመጀመሪያው ጀምሮ አነሳሳቸውን ለማጥናት፣ ብዙ ወደኋላ መመለስን ይጠይቃል። ብዙ የታሪክ ምሁሮችን በጉዳዩ ላይ ማዝመትና ማስማራትን የግድ ይላል። እንዲሁም ብዙ የሥነ-ልቡና ጠበብቶችንም፣ በድርጅቱ መስራቾችና መሪ ግለሰቦች ላይ የተቻላቸውን ያህል ጥናት አድርገው፣ የሥነ-ልቦና ችግራቸውን አውቀውና/ተረድተውላቸው እነሱንም በማዳን፣ አገርንም ለማዳን መጣር፣ ለነገ የማይለጉት ሀገራዊ ግዴታ ነው። ቀደም ብዬ በጠቀስኩት የሰውን ልጅ በሚፈታተኑ ከባድና አስቸጋሪ በሽታዎች፣ <u>የማንነት ቀውስና</u> <u>የዝቅተኝነት ስሜት</u> የሁለቱንም አደገኝነት በእኔ እይታ ለማሳየት ሞክሬአለሁ። እነኝህ ሁለት ከባድ በሽታዎች መድሃኒታቸውም የዚያኑ ያህል ከባድ ነው። ምክነያቱም መጀመሪያውንም መድሃኒቱ ራሱ የሚገኘው፣ በእነዚህ ከባድ በሽታዎች ሥር በወደቁ ሰዎች እጅ ላይ፣ በመሆኑ ነው። በሃገራችን ጥንታዊ፣ ባህላዊና እምነትን መሰረት ያደረጉ የቆዩ መድኃኒቶቻችን <u>ጠበልና ዱአ</u> ሲሆኑ፣ የእነኚህን ፍቱን መድሃኒቶች ፈውስነት ለመቀበል ራሱ፣ አሁንም የበሽተኞችን ፈቃደኛነት ይጠይቃል። በዘመናችን ደግሞ በሥነ-ልቡና ጠበብቶች አጠራር "የሥነ-አዕምሮ መታወክ" ላጋጠማቸው ሰዎች በሽታቸውን ለማከምና ለማዳን የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆን የሚችለው፣ አሁንም በዚህ በሽታ ሥር የሚማቅቁ ሰዎች፣ በሽታቸውን ሳይደብቁ፤ ሃኪሞቻቸውን እንደ ልብ ጓደኞቻቸው ተመልክተው፣ ታሪካቸውን ከመጀመሪያው ጀምሮ ለሃኪሞቻቸው ለማጫወት መድፈር መቻላቸው ነው። በእነኝህ ሁለት ከባድ በሽታዎች የተያዙ ሰዎች ይህንን ማድረግ ከተሳናቸውና ድፍረቱም ከሌላቸው፣ የበሽታው አንዱ ከባድ ምልክት ነውና

ሃላፊነቱ የበሽተኛው/ኞች ሳይሆን፣ በሽታውን ለማዳን የተሰለፉትና የሚሰለፉት ጠበብቶች አስገድደውም ቢሆን ህክምናውን መጀመር ይኖርባቸዋል ማለት ነው። አለበለዚያ ለሚያደርሱት ጥፋት ተጠያቂዎቹ በሽተኞቹ ሊሆኑ አይችሉም። እነርሱማ በሽተኞች ናቸውና። ለዚህም ነው በሃገራችንም የቆየው ባህል የበሽታውን ከባድነትና አደገኛነት እንደተረዱት ወዲያውኑ ፀበልም ሆነ ዱአ ወደሚሰጥበት ቦታ ሲያደርሱዋቸው፣ በሽተኞችን መጀመሪያ ላይ እግራቸውንና እጃቸውን አስረው ዱአውንና ፀበሉን በሥራ አከላታቸው እንዲሰርጽ ለማድረግ የሚጥሩት። በሳይንሱ ወይም በዘመናዊው የህክምና ዘዴ ደግሞ የበሽታውን አደገኛነት ከተረዱት በበሽታው የተለከፉትን ሰዎች አስቀድመው በማቀዝቀዝ/ በማደንዘዝ አስፈላጊውን መድሃኒት የሚጀምሩት።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ሆይ!

እኔ የህ.ወ.ሓ.ት/ወያኔ አለቆች ከፍተኛ የሆነ የማንነት ቀውስ እንዳላቸው የምረዳው፣ ብዙ የምናውቀውን፣ ያሳዩንና የምንመለከተውን ሁሉ ሳልዘረዝር፣ በቅርቡ ለትግል ተነሳንበት ሲሉት የቆዩትን አላማና እስከአሁን ድረስ የተጓዙበትን መስመር (እነደ ማንኛውም ወፈፌ) በየደረሱበት እያውገረገሩ ራሳቸውን በራሳቸው ጥያቄ ውስጥ በመክተት የእብደታቸው ሰለባ ሲሆኑ እንመለከታለን። እስቲ የነዚህን ሰዎች የእብደት አካሄድ ሁሉን ሳይሆን አንዳንዱን እንፈትሸው። ባሕረ ነጋሽ/ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አልነበረችም፤ ከነበረችም ኋላ ቀሯ ኢትዮጵያ ወይም "የአማራው ኩራኩር" ቅኝ ግዛት ስር ወድቃ ስትማቅቅ የኖረች ምስኪን "ሀገር" ነበረች። ስለዚህም እናንተ "ዳኝነትና ሽምግልና" የምታውቁት የዓለም መሪዎች ሁሉ፣ ባህረ ነጋሽ/ኤርትራ ራሱዋን ትችል ዘንድ በምናደርገው ተግባርና/ውሰኔ ፊታችሁን እንዳትነሱን ጫማችሁ ሥር ውድቀን እንለምናችኋለን ብለው "አሥመሪናን" አስመራ አድረጉዋት። አሥመሪና አሥመራ ቋንቋዋ አረብኛ፣ ተግባሩዋ አማርኛ፣ ልቧ አበሽኛ። እታይ ይባሓል እዩ እዚ ነገር - ይህንን ምን ትሉታላችሁ - ወገኖቼ! ቁ.1 የሥነ-ልቡና ደዌ ካልሆነ። ታዲያ ያን ሰሞን በነፃ ጋዜጦቻችን ላይ "ዘንድሮ" በሚል ርዕስ

> ሙሽሪት ኤርትራ ጎጆ ወጣሁ ካልሽን
> ለምን ከእኛው ጋ ተውሽ ቀበኛ ውሻሽን፣
> ጓዝ ማንሳትሽ ላይቀር ከዋለ ካደረ
> እንዴ መለስ ብለሽ ብትወስጅ ምናለ።

ተብሎ ነበር "ሀገር" የሆነች መስሎን። አይገርምም! ይህችም እድሜ ሆና ስንቱን አዬን። ግጥምዋን ያነብብኳት ዛሬ ከታገዱት ነፃ ጋዜጣቻችን ባንደኛው ላይ ነበር ስሙን ለጊዜው ባላስታውሰውም፤ የግጥሟ ባለቤት እንዳልሆንኩ ግን አረጋግጥላችኋለሁ። እስቲ ደግሞ ሌላውን እንመልከት።

የወያኔ አለቆች ትግሉን ሲጀምሩ "እነሳሳችን በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ መምታት የሚል ነውና ባህረ ነጋሽን ጥግ ካስያዝን፣ የትግራይን ህዝብ ደግሞ ነጻ አውጥተን የትግራይ ትግርኝ ሪፑብሊክ ማቋቋም ነው" ብለውን ያን ስንጠብቅ፣ አለፊው ሄዱና አይ! አሁንማ "አባይ ኢትዮጵያን" ማዶ ሆነን ስናያት ስላማለለችን ገፍተን እዚህ ደርሰናል፤ ግን ማንነታችንን እየፈለግን ነውና

ማንነታችንን እስክናገኝ ድረስ ፋታ ስጡን ብለው እርፍ። ይህንንስ ምን ትሉታላችሁ ቁ.2 የሥነ ልቡና ደዌ ካልሆነ።

የህ.ወ.ሓ.ት/ወያኔ ጉዶች "ስትጨቁነን ከነበረችው ኢትዮጵያ ተገላግለን የትግራይ የበላይነትን በመመለስ ዘውዱን እንደፋላን ብለው ተከታዮቻቸውን ጮቤ ሲያስረግጡ ኖሩና፤ የዋህ ተከታዮቻቸውን ባላሰቡትና ባልተጠበቀት ሁኔታ ደግሞ "ከሰለጠነችው ኤርትራ ጋር እንቀላቀላችኋለን" ብለው ልባቸውን በጠር ወግተው አሳዘኗቸው። ይሄ ታዲያ የወያኔ መሪዎች የማንነት ቀውስ ካልሆነ ምን ሊባል ይችላል ወገኖቼ? ቁ.3 የሥነ-ልቡና ደዌ ማለት የሄ ነው።

ይህ ክፉ በሽታ መድሃኒቱ ካልተገኘለት ቀውሱም ያን ያክል ነውና "ትግራይን" ወስደን መቀላቀላችን አይቀርም ብለው ሲነግሯቸው ልባቸው የተሰበረ ተከታዮቻቸው፣ በሃዘን ተጎድተው ኩርምት ብለው እያለ፣ ሥጋዉን ሰጥቶ ሙዳውን እንዲሉ፣ የባድመ ነገርም ይታሰብበት ብለዋቸው ቁጭ። ይሄ ታዲያ የጤና ነው፤ ነው የምትሉኝ? እኔ አንጃ አላህ ይወቅላቸው።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ሆይ! በእንዲህ አይነት የማንነት ቀውስና የዝቅተኝነት ስሜት የሚዋዥቁ ሰዎች በርግጥም የታመሙ ናቸውና ህመማቸው ቀላል ባለመሆኑ፣ በቅድሚያ ራሳቸውን፣ በኋላም ቤተሰባቸውን፣ እልፍ ሲል ቤተ ዘመዳቸውን፣ከፍ ሲል ማህበረሰብን፣ ህብረተሰብንና በአጠቃላይ ህዝብን፤ በመጨረሻም ሀገርን ያክል ነገር ምን ያህል እንደሚፈታትኑና እንደሚጎዱ፤ ዝም ከተባሉና ከተለቀቁ ደግሞ ጭራሽ አገርን ይዘው ሊጠፉ እንደሚችሉ፣ ከዚህ በላይ ማስረጃ ምን ይገኛል። በዚህ ከባድ በሽታ ግለሰቦች ሲታመሙ ሀገር በአጠቃላይ እንዴት እነደሚታመም፣ አንድ ማስታወሻ ላቅርብ! የማነትን ቀውስ ገላጭ። እጠቅሳለሁ፥

> መለስ ማንና ምን ሆነው ነው ዛሬ የኢትዮጵያ አርበኛና ጥቅም አስጠባቂ ሆነው ራሳቸውን ለማቅረብ የሚሞክሩት? ዛሬ በትግራይ ውስጥ ያላቸው ድጋፍ እየመነመነ ሲሄድ ፊታቸውን ወደ ሌላው ብሔረሰብ እያዞሩ መሆኑ በግልጽ ይታያል።
>
> "የትግራይን ህዝብ፤ እንኩዋን ከእናንተ ተወልድኩኝ" ብለው በመናገራቸው ጥያቄ ሲበዛባቸው ጊዜ ከናካቴው "በእሳት ከተፈተነው፤ ተፈትኖ ጨርቅ ሳይሆን ወርቅነቱን ካስመሰከረው ህዝብ በመወለዴ እኮራለሁ፤ በዓለም ላይ ሌላ ወርቅ የሆነ ሕዝብ የለም ማለቴ አይደለም።" ብለው ከቀድሞ አቋማቸው ለማፈግፈግ ሞክረዋል። እንደገና በ1989 ይህንን አባባል እንዲያብራሩ ሲጠየቁ፤ "ይህ አባባል ንስሃ የምገባበት አይደለም። የትግራይ ሕዝብ በእሳት ተፈትኖ ነው የወጣው። ወርቅና ጨርቅ በእሳት ይለያል። የትግራይ ሕዝብም በእሳት ተፈትኗል። ጨርቅ እንዳልሆነም አስመስክሯል" በማለት የቀድሞ እምነታቸውን አረጋገጡ። አባባሉ ኤርትራዊ አይደለሁም ለማለት ነው።(ከዳዊት ወ/ጊዮርጊስ ክህደት በደም መሬት መጽሃፍ፣ ገጽ 445)

ከዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ሌላውን እንቆቅልሽ ነገር ደግሞ ላምጣ!

> <<ወይዘሮ ዓለማሽ ገ/ልዑል የመለስ ዜናዊ እናት ናቸው። የታወቁት የፀአዘጋ ተወላጅ፣ የሠራዬው አርበኛ የራስ ኪዳነ ማርያም የቅርብ ዘመድ ናቸው። በግልጽ በሪፈረንደሙ ወቅት ለኤርትራ "ነፃነት" ድምጽ ሰጥተዋል። በእንደዚህ ያለ ምክንያት ብዙ ኤርትራውያን ከአዲስ አበባ ሲባረሩ፣ ወ/ሮ አለማሽ በግዴታ አልሄዱም ነበር፤ ሞት ወሰዳቸው እንጂ። ይህንን ከአገር የተባረሩት ኤርትራዊያን ያውቃሉ። በኢትኦጵ መጽሔት እንደተገለጠው።

" አንዲት ኤርትራዊ እናት ወደ ኤርትራ ሲሽኙ አልሄድም ብለው ያስቸግራሉ። በተለይም ወደ ኤርትራ ለመሄድ ቀይ መስቀል ባዘጋጃቸው አውቶብሶች ላይ እንደሌሎች ኤርትራዊያን እንዲወጡ ሲጠየቁ፣ ፈጽሞ አልወጣም ብለው እሪታቸውን ያቀልጣሉ። <ሪፈረንደም ተሳትፈሻል፤ መሄድ ግዴታሽ ነው> ብለው ሲነግሯቸው <ሪፈረንደም የመረጥኩት ከዓለማሽ ጋር ሄጀ ስለሆነ ከእሷ ለምን ትለዩኛላችሁ?> በማለት ላለመሄድ እንባቸውን እያፈሰሱ ያማርራሉ።"(ኢትኦጵ፣ ቅፅ 1፣ቁ.8፣ ጥር 1992)»>

ሌላውን አስገራሚ ታሪክ ደግሞ ከዚሁ ከዳዊት ወ/ጊዮርጊስ መጽሃፍ ልጥቀስ።

የኢሳያስ አፈወርቂ እናት ወ/ሮ አዳነች በርሄ የአድዋ ተወላጅ ናቸው። ኑሯቸው ግን በአብዛኛው ኤርትራ ነበር። የኢሳያስ አባት አቶ አፈወርቅ አብርሃ (<ቂ> በኋላ ነው የገባችው) ጡረታ እስከወጡበት ድረስ በአዲስ አበባ፣ በኋላም መቀሌ በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመሬት ይዞታ ክፍል፣ ይሰሩ ነበር። የተወለዱት አዲ ታንኳምላሽ፤ ተምቤን ውስጥ ነው። የኢሳያስ አጎት ማለትም የአባቱ ወንድም ደጃዝማች ስለሞን አብርሃ ይባላሉ። የወሎ እንደራሴ ሆነው በንጉሡ ጊዜ ያገለገሉ፣ የታወቁ ሰው ናቸው። የደጃዝማች ስለሞን እናት ትውልዳቸው አጋሜ አውራጃ፤ አፋሹም ወረዳ ነው። አባታቸው ደግሞ ከተምቤን ነበሩ። ደጃዝማች ስለሞን አብርሃ በጠቅላላ ሶሥት ወንድሞች ነበሯቸው። የኢሳያስ አባት አቶ አፈወርቂ አብርሃ፣ የባህር ሃይል ካፒቴን መኮነን አብርሃና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይሰሩ የነበሩት አቶ ሐጎስ አብርሃ ይባላሉ። ኢሳያስ ያደገውና የተማረው፤ ወሎ ደሴ ከተማ ነው። ከዚያ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገባ። ከዚያ ነው ወደ በርሃ የወጣው። ፕሬዚዳንት ኢሳያስ በአባቱም በእናቱም ሥረ መሰረቱ ትግራይ ነው።

(ክህደት በደም መሬት ከገፅ 447-448)

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ! እውነተኛው ታሪክ ይሄ ነው። ታዲያ እነኝህ የወያኔ አለቆች ሊሰሩልን ያሰቧት "አዲሲቱ ኢትዮጵያ" ከየት እንደሚያመጧትና መነሻዋም የት እንደሆን እስካሁን አልገባኝም፤ ሊገባኝም አይችልም። የእነርሱም ነገር እንዲሁ። አጃኢብ ይላል የሐረር ሰው! እና ቁ.4 የሥነ-ልቡና ደዌ ይህ ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ለማንኛውም ወገኖቼ! አገራችን ኢትዮጵያ በነዚህ ልጆች እጅ ናትና፣ የሀገራችንን እጣ ፈንታ ከነኝህ በሽተኞች እጅ አውጥተን እናድናት ዘንድ፣ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያውያን፤ በተለይ ደግሞ በውጭ ለምትኖሩ ትግርኛ ተናጋሪው ማ/ሰብ፣ ከእኛ ከወገኖቻችሁ ጋር አብራችሁ በመቆም አገራችንንና ህዝባችንን እንድናድን የተጣለብን ከባድ ሃላፊነት ነው። በውጭ የምትኖሩ የትግርኛ ተናጋሪው ማህብረሰብ ምሁሮች በተለይ፤ ከማኘኛውም በላይ ለዚህ ከባድ ሀገር አድን ግዳጅ ከመቼውም ጊዜ በላይ በአደባባይ እየወጣችሁ፣ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ታሰሙ ዘንድ ከባድ ኃላፊነት ከፊታችሁ ተደቅኗል።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር!
የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ያለቅደመ ሁኔታ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ቸር ይገጠመን